# ገባች ! ወጣች ! ቦለቼ ! ቦለቼ !

ሚያዝያ 12 ቀን 2010 ዓም

(20-04-2018)

እለቱ ቅዳሜ ነው፤የአስራ አምስት ዓመት ልጅ ሆኜ ነው፣ ከአንድ ዘመድ ያገኘኋትን አንድ ብር ስጦታ፣በዛን ጊዜ አንድ ብር ማለት ብዙ ገንዘብ ነው፣ያውም ለተማሪ!በደስታ እየፈነጠዝኩ የማውልባትን ቦታ አከፋፍዬ ለመጠቀም ወሰንኩ።በሃምሳ ሳንቲም ፊልም ለማዬት ሲኒማ እራስ፣በስሙኒ ሰላም ሻይቤት አንድ ሰሃን ፉል ከሶስት ዳቦ ጋር፣ በ 15 ሳንቲም ከጓደኞቼ ጋር በራድ ሻይ፣በአምስት ሳንቲም ሲኒማ ቤቱ ደጃፍ ኦቾሎኒና በቀረችዋ አምስት ሳንቲም ሶስት ባለጦርማስቲካ ለመግዛት አደላድዬ ከሁለት ጓደኞቼ ጋር ከዩሃንስ ሰባራው ባቡር ከተባለው ሰፈር ተነስተን መንገዱን በጣልያን ሰፈር ውስጥ ውስጡን አቋራርጠን ወደ መርካቶ አመራን።

ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ ድልድይ ላይ ስንደርስ፣ብዙ ሰው ከቦ አየን፤እየተጠጋን ስንመጣ አንዱ ገባች ወጣች!፣ ቦለቼ ቦለቼ! እያለ ድምጹን ከፍ አድርጎ ይጮሃል፤ሌሎቹ ደግሞ እድልድዩ ላይ ተቀምጠው ድብድብ(ባራ) ይጫወታሉ።በሁለቱም አቅጣጫ ኪስ ለማራቆት የቆረጡ ወረበሎች ከባቢውን ተቆጣጥረውታል።የሰው መሰባሰብ ቀልባችንን ስቦት ለማዬት ስንጠጋ፣አንዱ መሬት ላይ ተቀምጦ ፣ቁራጭ ካርቶን አንጥፎ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው የዳማ ጠጠርና ኩባያ ይዞ በየተራ ጠጠሩን በኩባያው እየሸፈነ፣ ገባች! ወጣች!ቦለቼ፣ቦለቼ እያለ ይጮሃል። ተወዳዳሪ የተሸፈነችውን ጠጠር ቀለሟን በመናገር ገንዘብ እየመደበ ይወዳደራል።ያ አጭበርባሪ አጫዋች በማምታታት ኩባያውን ሌላ ቀለም ካለው ጠጠር ላይ ያስቀምጥና ሲነሳ ተወዳዳሪው ከመረጠው ቀለም ይለይና ገንዘቡን ይበላል።በዚህ መልኩ በጨዋታው ወጥመድ ውስጥ የገባው ሁሉ ሳያተርፍ በኪሳራ ይሰናበታል። ጨዋታው ሕገወጥ በመሆኑ ፖሊስ ይከለክላል፤አጫዋቾቹንም ከያዛቸው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይወስዳል።ከዚህ ለማምለጥ አንዱ የቡድኑ አባል የሆነው ፈንጠር ብሎ ፖሊስ መምጣቱን ይቆጣጠራል።ጨዋታው በደራበት ሰዓት ላይ ፖሊስ ከመጣ ያ ቃፊር ቀንዶ! ቀንዶ!(በእኛ ጊዜ ፖሊስን ቀንዶ ወይም ኡጂ እያልን ነበር የምንጠራው) ብሎ ሲጮህ ቁማርተኛው ሁሉ የከበበውን የሰው አጥር ጣጥሶ እግሬ አውጭኝ ብሎ ወደ አሜሪካን ግቢ ይሰወራል። ፖሊሶቹ የከበበውን ተመልካች ወይም ተጭበርባሪ በያዙት አጭር ዱላ እየጎሰሙ ይበታትኑታል።

ፖሊሶቹ ከቦታው ሲርቁ እነ አጅሬ ተመልሰው ከያቅጣጫው ይመጡና ጨዋታው ይጀመራል።ለማስመሰል እርስ በርሳቸው የመጫወትና የማሸነፍ ድራማ ይሰራሉ።ሚስጥሩ ያልገባው የኔ ቢጤ አተርፍ ባይ ለጉዳዩ የያዛትን ሳንቲም አስረክቦ ባዶ እጁን ይቀራል።እኔም ለዛ ብዙ ትካር የመደብኳትን ብር ቀስ በቀስ እልህ በመግባት ግማሿን አስረከብኩ።ዕድሜ ለጓደኞቼ፣ የዛን ጊዜ ጓደኛ ያለችውን አብሮ ይካፈላል፣ሲኒማውም ፉሉም ሻይውም ሳይቀር ያሰብናትን አድርገን እቤታችን ገባን።ሁለተኛ የነዛን ዱርዬዎች ተንኮል በሩቁ እንጂ ቀርቤ ሳላይ ካገሬ ወጣሁ።

አሁን ከብዙ ዓመታት በኋላ ተመሳሳይ ገባ ወጣ!ቦለቼ ቦለቼ የመሰለ በአገር አቀፍ ደረጃ በሚፈጸም ፣ የፖለቲካ ቁማር ጨዋታ ለማዬት በቃሁ። የቁማሩ ጨዋታ በቡድን መልክ የሚካሄድ ሲሆን የጨዋታው ስም አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚለው ቁማር ነው። ዋናው የጠጠሩ ና የኩባያው ባለቤት፣ግባ ውጣ እያለ የሚያዝና የሚያጭበረብረው ወያኔ የተባለው ቡድን ነው።ጠጠሮቹ የሚለዩበት የሚሸከሙት ባንዲራና የሚጠሩበት ስማቸው ኦህዴድ፣የደቡብ ህዝቦች፣የብሄረአመራ ሲሆን የጋራ መጠሪያ ስማቸው ኢሕአዴግ የሚለው ነው።በዚህ ጨዋታ እንደ መርካቶው ገባች ወጣች!፣ቦለቼ ቦለቼ ቁማር በኩባያው ውስጥ ቦታ እየቀያየሩ የሚንቀሳቀሱትና የሚያምታቱት እነዚሁ የፖለቲካ ጠጠሮች ናቸው።የሰሞኑ ቁማር ሕዝብ በትግሉ የሚፈልገውን ለማግኘት ሲሰለፍ ፣ትኩረቱን ለማስቀየር የሚረዳ ማወናበድ በመጠቀም ጥቅም የማያገኝበትን ጠጠርና ፣ጠጠሮች ከቦታ ቦታ በመቀያዬር ለውጥ መጣልህ፣ልትጠቀም ነው ይሉታል።ሕዝቡም እውነት እዬመሰለው በጉጉትና በተስፋ ይጠብቃል።በገሃድ ግን ሲታይ ላም አለኝ በሰማይ ሆኗል፤እንደመርካቶው ድብ ድብ ጨዋታ ፎረረ! ሲባል መጃጃሉን እያወቀው መጥቷል።

ላለፉት 27 ዓመታት በልዩ ልዩ የስልጣን ቦታዎች ሕዝቡን መከራውን ያሳዩት የነበሩት ፣የጥፋቱና የወንጀሉ ተጠያቂዎች የሆኑት የኢሕአዴግ ባለስልጣኖች አሁን ቆብ እየቀያየሩ በሌላ ሹመት ላይ እንዲቀመጡ ተደርጓል፣ቦታ መቀያየሩን በለውጥ ስም በሚስተጋባው የውሸት ወሬ ህዝቡ እንዲወናበድ ሆኗል። አልወናበድም፣ለውጥ የለም፤ የሚለው ክፍል ዛሬም እንደ ትናንቱ እየተገደለ፤እየታፈሰ ነው።ወይም የለውጥ ጠላት ተብሎ ተሰይሟል። በኢሕአዴግ ጠጠሮች መካከል የተደረገውን የቦታ መቀያዬር "ሰላማዊ ሽግግር" እያሉ ትርጉሙን በማጣመም፣ በተቀናቃኝ ሁለት ፓርቲዎች መካከል በተደረገ የሕዝብ ምርጫ ውጤት የተደረገ የስልጣን እርክክቦሽ በማስመሰል ነጋሪት ይጎሽማል። የአንድ ድርጅት አባላትን የቦታ መቀያዬርና መውጣት መውረድ የለውጥ ሂደት ነው ተብሎ ይለፈፋል።ሌላውም የቁማር ጨዋታው ከቦ የሚታዘበው እያጨበጨበ በነዛ

አጭበርባሪዎች፣በወጣች ፣ገባች! ቦለቼ! ቦለቼ! እንደሚዘረፈው የዋህ ሆኖ የትግል መንፈሱን እየተሰለበ ነው።

ዶር/ኮሎኔል አብይ አህመድ፣በጠቅላይ ሚኒስቴርነት የተሰዬመው የኢሕአዴግ ኩባያ፣በስሩ ያሉትን ጠጠሮች አቅፎ ጨዋታውን እያደራው በመሄድ ላይ ነው ። በተለያዩት አካባቢዎች የሚኖረው ሕዝብ በሚናገረው ቋንቋ እየተናገረ፣የሚለብሰውን አለባበስ እየለበሰ የሕዝቡን ልብ ለማሟሸሸና ከፐያቄው ለመሸሸ የማያደርገው ጥረት የለም፤ጥረቱ ግን የተጠበቀውን ያህል ውጤት ባያመጣለትም በጥቂቱም ቢሆን ደካሞችን አጃጅሎበታል።በየቀኑ ከድጡ ወደ ማጡ እዬገባ በመሄድ ላይ ነው።ዛሬም እንደ ትናንቱ ሕዝብ በጦር ሃይል ቁጥጥር ስር የዋለ የቁም እስረኛ ነው።ለመቃወምም ሆነ ለመጠዬቅ መብት የለውም።በዛሬው እለት በጎንደር ከተማ የጠ/ሚኒስትሩን ጉብኝት ተከትሎ የታዬው ማጭበርበር  የዚህ ነጸብራቅ ነው።ሌላው ብዙሃን ከቦታው እንዳይደርስ ታግዶ ደጋፊዎች ብቻ ተገደውም ይሁን ወደው የተሰበሰቡበት ትያትር ነው።በየቦታው የጎሳው ግጭት ቀጥሏል። ዜጋ ቤቱ እየፈረሰበት ፣በግፍ እየተቃጠለበት ቦታውን በመነጠቅ ለሃብታም እየተቸበቸበ ነው።አሁንም ስርዓቱ በጎሳና ቋንቋ ስሚንቶና ድንጋይ በተገነባ የክልል ግምብ የተከለለ፣ኢትዮጵያም ለመፈራረስ ታቅዶ በተዘጋጀ ቦምብ የተከበበች  የፈንጂ ወረዳ ነች።  ሰው በፈለገው ጊዜና ቦታ እንደልቡ በነጻነት አይንቀሳቀስም። ምንም እንኳን በረራው ካመለጠው በኋላ ዘግይቶ ቢፈቀድለትም፣በዛሬው እለት በውጭ አገር ተቋም ግብዣ ሁሉን ነገር አሟልቶ ቦሌ አየር ማረፊያ ለመውጣት ሲቃረብ በጋዜጠኛው በአቶ እስክንድር ነጋ ላይ የደረሰው ወከባና እገዳ  እራሱን የቻለ ማስረጃ ነው።ይህስ የለውጡ አካል ወይንስ የቁማሩ የገባች ወጣች ማምታታት ስልት ይሆን?

የወደፊቱ የቁማር ጨዋታ ደግሞ ኢሕአዴግ የሚለውን የግንባር  ጭንብል አውልቆ በአንድ የፖለቲካ ስምና አደረጃጀት ለሚመጣው ምርጫ ለመዘጋጀት በሁሉም መስክ የበላይነቱን ይዞ በመጠቀም ጫና መፍጠርና  ስርዓቱን ማስቀጠል ይሆናል።በዚያ መልክ ወንጀለኞቹ፣ዘራፊዎቹ፣ገዳዮቹ በሰሩት ወንጀል ሳይጠየቁ አንቱ ተብለው እየተወደሱ ይኖራሉ ማለት ነው።በተቃዋሚው ጎራ ያለው በጥገና ለውጥ መሞዳሞዱንና መፍረክረኩን  ትቶ፤ የነአብይን ገባች ወጣች፣ቦልቼ ቦልቼ ቁማር ማመኑን ትቶ፤ የቆመለትን ዓላማ በቅጡ ግልጽ አድርጎ ቁርጠኛ ሆኖ መታገል ይኖርበታል።የአገርን አንድነት የሚፈታተነው ትልቁ ችግር፣የጎሳው ፖለቲካ ገና አልተነካም።ሁሉም ጥያቄ ሕገመንግስት ብለው ባረቀቁት አገር አፍራሽ፣ ሕዝብ አጫራሽ በሆነው የጥፋት ማኒፌስቶ መሰረት የሚታይ ነው። በዛሬውም እለት የወልቃይት ማንነት ጥያቄ በዛው አንጻር ይፈታል ሲል ጠ/ ሚኒስትር አብይ መልስ ሰጥቷል። የሌላውም ጥያቄ እንዲሁ።

ኢሕአዴጎች እስካሉ ድረስ ገና ብዙ የቁማር ፣የገባች ወጣች፣ቦለቼ ቦለቼ ጨዋታ እናያለን።ገና ብዙ እንጭበረበራለን።ያንን የማንፈልግ ከሆነ መፍትሄው ከቁማርተኞቹ መራቅና ቁማርተኞቹንም ማሶገድ ብቻ ነው።

አገሬ አዲስ